# በኑሮ መቃወም!



ዓለማየሁ ገላጋይ

ለጠራረገን ሁሉ መግበስበስ የዚህ ዘመን ዓይነተኛ በሽታ ነው። የተገደድንበትን ነገር የምንተገብረው እስካልተገደድንበት ድረስ አፈግፍገን ነው። «እጃችሁን ስጡ» ስንባል፣ እግራችንን ጨምረን እናስረክባለን። «አደባባይ አትውጡ» ከተባልን ካልጋችን ላለመውረድ እንወስናለን። የፍርሃት «ኔትወርክ» ዘርግተናል። ለጭነት ተመቻችተናል፣ «ዱላ» የያዘ ሁሉ ይነዳናል። ያፈጠጠ ሁሉ አንገት ያስደፋናል...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ለጠራረገን ሁሉ መጠራረጊያችን ግድ ቢሆን እንኳን መግበስበሳችን ላይ እናስብበት። የተገደድንበትን ነገር ስንተገብር እስካልተገደድንበት ድረስ ማፈግፈጋችንን እንታዘብ። የተጠየቅነውን «እጃችንን» ስንሰጥ፣ ሳንጠየቅ ያስረከብነው «እግራችን» ይቆጨን። አደባባይ አለመውጣትና ካልጋ አለመውረድ ምን አንድ እንዳደረጋቸው አስበን በራሳችን ላይ እንሳቅ። ጊዜ ለሰጠው «ዱላ ያዥ» ብቻ ስንነሳ፣ ለአስመሳይ ባለስልጣን አንገታችንን አንድፋ....

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...አደባባይ ባይሆንልን ቤታችንን ነፃ እናውጣ። «እኔና ቤቴ ግን በኢትዮጵያ አንድነት እናምናለን» ብለን እንፃፍ፣ ዕፊን ግድግዳችን ላይ እንለጥፍ። በአደባባይ ያጣነውን ነፃነት በቤታችን ውስጥ እንቀዳጅ፣ የተዋረደውን ባንዲራ በቤታችን ከፍ-ከፍ እናድርግ። የተሻረውን ካርታ ሳሎናችን ውስጥ እንሹም፣ ኤርትራና ኢትዮጵያን እንቀላቅል። የቤኒአሚሩ ጉብል ፓስተር አሁን የት ነው? እንፈልገው፣ ከሐረር ፓስተር አጠገብ የአስመራ ፓስተር አልነበረም? የት ጣልነው? ለምን? መግበስበስ ይሄ አይደለም? ከጥንቷ አገራችን ሲያባርሩን፣ ስለምን አገራችንን ከልባችን እናባርራለን? መከፋፈሉን ከጠላነው «ክልል» ማለትን አፋችን ውስጥ ማን ከተተው? ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉልን፣ አፋርን.... ክልል አድርጎ ቤታችን ምን አስገባቸው?...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...እንኳን መንግሥት፣ ሴጣን... እንኳን ሴጣን ፈጣሪም ቢሆን በቤታችን፣ በልባችን፣ በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን ለማዘዝ ፈቃዳችንን ይሻል። ደጃፋችንን ሲቆረቁር ካልከፈትን፣ ወደውስጥም እንዲዘልቅ ካልጋበዝን የመኖሪያ ልዕልና አይደፈርም። እዚያ ያልተገበርነው ነፃነት፣ እዚያ ያላስጠበቅነው መብት... የት? በጉዳና የማይታሰበውን ሠላማዊ-ሠልፍ ከሣሎን እስከመኝታ ቤት እናካሂድ፣ ለገገርዎች የፈራነውን ለልጆቻችንና ለትዳር አጋሮቻችን እንፈክር ቤታችንና ልጆቻችን የመጪው ዘመን እውነታ ማህደር ይሆናሉ - ቢያንስ።

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...እነሱ፣ ገገርዎቹ የሚጠላላ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሌት-ተቀን ይለፋሉ። እኛ የሚዋደደውን ማህበረሰብ ለማቆየት ቢያንስ በቤታችን ምን አደረግን? እራሳችንን እንጠይቅ! ሲለያዩን፣ ያለመለያየት ዕቁብ ጠጣን? ሲነጣጥሉን ያለመነጣጠል ዕድር መሰረትን?

**...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ... ...እንኳን መንግሥት፣ ሴጣን... እንኳን ሴጣን ፈጣሪም ቢሆን በቤታችን፣ በልባችን፣ በመንፈሳችን፣ በነፍሳችን ለማዘዝ ፈቃዳችንን ይሻል። ደጃፋችንን ሲቆረቁር ካልከፈትን፣ ወደውስጥም እንዲዘልቅ ካልጋበዝን የመኖሪያ ልዕልና አይደፈርም**

ጠላት ሲያደርጉን በጋብቻ ተዛመድን? ሲያቃቅሩን የአንድነት ፅዋ ማህበር አቋቋምን?... ወይስ ዓይን-አባት ከብሔራችን አጨን? የጡት አባታችንን ከቀያችን ሙጥኝ አልን? ጉዲፈቻ ከወንዛችን ፈለግን? ከጐሣችን አጨን? አማጫችንስ? ሽምጋያችንስ? ሽርካችንስ?... ከጐጣችን? «እጃችሁን ስጡ» ስንባል እግራችንን ጨምረን ማስረከብ ማለት ይሄ ነው።

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ፖለቲካዊ ክፋ ሥራን፣ በኢትዮጵያዊ ጨዋ ተግባር እንቃወም። ፋታ ያጣውን አናራውጥ፣ ኑሮ የከበደውን አንጫን፣ መግቢያ የሌለውን መድረሻ አናሳጣ፣ ጊዜ የጣለውን አንርገጥ፣ ከከሰረው አናትርፍ፣ የወደቀው ላይ «ምሣር» አንሁን... የዚህ ዘመን ፖለቲካ «እርስ - በእርሱ» ላይ የተመሰረተ ነው። መጣደፍን ሲፈጥሩልን እርስ በእርስ እንረጋገጣለን፣ ጠላትነትን ሲያቃርቡልን እርስ በእርስ እንባረራለን፣ እጥረት ሲያመጡልን እርስ በእርስ እንነጣጠቃለን፣ ጥርጣሬ ሲዘሩብን ጠላትነት እናበቅላለን፣ «ጃስ» ሲሉን እንነካከሳለን፣ ሲያጋጥሙን እንቧቀሳለን...

...ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ቤታችን፣ ልባችን፣ መንፈሳችንና ነፍሳችን ከዚህ ይፅዳ። ነጋዴ ነን? አላግባብ አናትርፍ፣ አከፋፋይ ነን? ተፈጥሯዊ ያልሆነ እጥረት አንፍጠር፣ መምህር ነን? ተማሪ ከተማሪ አናበላልጥ፣ ስፖርተኛ ነን? ብሔር አንወክል፣ አርቲስት ነን? ዘር ከዘር የሚከፋፈል ድግስ አናድምቅ፣ አሰሪ ነን? ሥራን ብቻ ማዕከል እናድርግ፣ ቤት አከራይ ነን? ለተከራይ እንዘን፣ ገበሬ ነን? ሰው በቆርቆሮ ቤት አንቀይር፣ ኮንትራክተር ነን? ጥራት አንቆነጣጥብ፣ ጋዜጠኛ ነን? ለሕዝብ ብቻ እንቁም፣ የሕግ ባለሙያ ነን? ፖለቲካ አንቀላቅል፣ የምክር ቤት አባል ነን? በእንቅልፍ ልብ እጃችንን አናውጣ...

...ዛሬ - ዛሬ...

...እውነታ ተገልብጧል። ሌባ ይንጐባለላል፣ ተዘራፊ ያፍራል። የቀማኛ ልጅ ደረጃ አግኝቷል፣ በላቡ የሚኖር አባት ያለው መግቢያ አጥቷል። አደባባይ የነውረኞች ሆኗል፣ ጨዋ መሸሸጊያ ጓዳ አጥቷል። አገራቱ ከነውር የተገነባ ጎጆ ሆናለች። አድርባይ ጉልላት፣ አላዋቂ ክፍክፋት፣ ወሮበላ መርገፍ፣ አልጠግብ ባይ ደጃፍ... ሆነዋል። የዚህ ዘመን መሠረት ግን እኛ ነን። እንዴት?

እንዴትማ... የመኖር ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ የሚከማች ሀብት ሁሉ በማህበረሰብ ዘንድ የተሻለ ሆኖ የመታየትና የመከበር ፍላጐት ነው። «የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው» ሆነናልና የሀብት ጀርባ ማጥናት ትተናል። ለሌባ እንጎናበሳለን፣ ለቀማኛ ወንበር እንለቃለን፣ ለዘራፊ እንሽቆጠቆጣለን። ሌብነት እንደማሳለጫ የማቋረጫ መንገድ ብቻ ሆነ።

......ቢያንስ ከዛሬ ጀምሮ...

...ሌባን ማቆላመጥ ይቅር፣ አይናችን ይብላው፣ ሚስቱ ፊት ይሸማቀቅ፣ ልጁ ፊት ይሳቀቅ፣ እማት ደጅ አይድረስ፣ ከሰው ጋር አይቁረስ... ቤታችን፣ ልባችን፣ መንፈሳችን፣ ነፍሳችን... ብሎም አገራችን የሚፀዳው እንዲያ ነው። ያልተገባን ባደባባይ ባይቻል በኑሮ በመቃወም። □